ብሉበርድ ት/ቤት የ8ኛ ክፍል የመጀመሪያው የአማርኛ ሞዴል ፈተና /2ዐ15 ዓ.ም/

ሰነ - ቃል በመነገር፣በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፍያ ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የሕይወት መልኮችን መግለጫ ኪነ- ጥበብ ነው። ይህ ኪነ - ጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት፣ ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥቅምና የገጠመኞቹም ማንፀባረቅያ ነው። ይህ ቃላዊ ጥበብ በተለይ ፊደል ቀርፀው በፅሑፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነትንን ምንነትን፣እምነትን፣የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን አጠቃላይ የዓለም አመለካከትን ቀርሶ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው የሚና ከፍተኛ ነው።

በስነ- ቃል ህዘቦች ማንነታቸውን ያሳውቁበታል። የዘርያቸው አመጣጥ ይተርኩበታል ስለ አካባቢያቸው በአጠቃላይ ስለአለማቸው ያላቸውን ፍልስፍና ይቅርፅበታል። ወግና ልማዳቸውን አጠናክረው የሚቆዩበት ዋነኛ መለያቸውም ነው። ህዘን ደስታቸውን ምኞት ተስፋቸውን ፍቅር ጥላቻቸውን ድል ሽንፈታቸውን ድጋፍ ተቃውሞአቸውን በአጠቃላይ የህይወታቸውን መልኮች ያንፀባርቁበታል። ታሪካቸውን ለተከታዮቻቸው በማስተላለፍ ረገድ እና የዝርያቸውን ተከታታይነት ያረጋግጡበታል። ሰናይ የማሏቸውን ማህበራዊ እሴቶችና ልማዶች ተጠብቀውና ተከብረው እንዲቆዩ፣ እኩይ የሚሏቸው ደግሞ እንደወገድ ያደርጉበታል። በአንድ ማህበረሰብ ላይ የደረሱ አስከፊ ሁኔታዎች ፣የተፈጥሮ አደጋ፣ስደት፣ርሀብ ፣ወረርሽኝ ፣ ጦርነት፣ የመሳሰሉት ኑሮን አናጊ አጋጣሚዎች ሲደርሱ በስነ - ቃል ይገለፃሉ ይታወሳሉ። ማህበረሰቡ ለዚህ አስከፊ አጋጣሚዎች የነበረው አመለካከትን የደረሰበት ጉዳይ በስነ- ቃሉ አማካይነት ተቀርፆ ለተከታዩ ትውልድ ይተላለፋል።

ስነ - ቃል ምንጭ የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጠመኞች ናቸው። በተለይ ከጥንታዉ የአኗኗር ዘይቤ ብዙ ባልራቁና ባልበለፀጉ ማህበረሰቦች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ በሚከሰቱ የተለያዩ ግንኙነቶች ምክንያት አያሌ ስነ- ቃሎች ይፋሰሳሉ።

በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በየወቅቱና በየዘመናቱ የሚወሩት ተረቶች በአምልኮ ስነ- ስርዓቶች ላይ የሚደረደሩት ውዳሴ አምልኮትና ዝማሬዎች በእርሻ፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ በሌሎች መሰል ህይወት ደጋፊ ስራዎች ላይ የሚዜሙና የሚነገሩ ስነ- ቃሎች በኩበት ስምሪት ጊዜ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች በቀብር ስነ- ስርዓትና ህዘን ላይ የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞች በኩበረ በዓላት፣በሰርግ፣በልጆች ጨዋታ ላይ የሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፈኖች በደቦ፣በእድር፣በእቁብና በመሳሰሉት አሰባሳቢ አጋጣሚዎች ላይ የሚሰነዘሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሰዎች በሚገናኙባቸው አጋጣሚዎች የሚነገሩ ወጐች ቀልዶች አፈ ታሪኮች እና ሌሎችም ስነ- ቃሎች ማህበረሰቦቹ ስለራሳቸው ስለ ሰው ልጅ ስለ አካባቢያቸው እና ስለ አለም ያሏቸውን አመለካከት እና የህይወት ፍልስፍናዎች የሚያንፀባርቁ ናቸው።

ከስነ ቃል ባህሪያት አንዱ አመንጭውን ወይም ደራሲውን ለማወቅ አለመቻሉ ነው። አንድን ተረት ወይም ቀልድ ወይም ባህላዊ ዘፈን እገሌ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የተረተው ወይም የተናገረው ወይም የዘፈነው ብሎ ዛሬ በደራሲነት አንድን ሰወ ለወጥቀስ አይችልም። አፈጣጠሩና ክንውኑ በጋራ በመሆኑ ባህላዊ ምግባር ለግለሰቡ ትኩረት አይሰጥም። ስነ- ቃሉም ሀብትነቱ የማህበረሰቡ ነው። ሰለዚህ የአቀንቃኝ ወይም የፈጣሪው ወይም ቡድን ማወቅ አይቻልም። ስነ- ቃሉን ሲነገር ወየመ ሲዜም ሰምቶ ለማስታወስ መልስ ለሌሎች ለመንገር ወይም ለማዜም የቻለ የማህበረሰቡ አባል ካንዱ ወደ ሌላው ሊያስተላልፈውና ለጊዜው ባለቤቱ ለመሆን ይችል ይሆናል። ከዚህም የተነሳ ነው ስነ - ቃል የህዝብ ሀብት ነው እየተባለ የሚነገርለት። የባህሉ ሰው የሆነ ሁሉ ችሎታም ካለው ከመተረትና ከማዜም የሚያግደው አይኖርም። ምንም እንኳ የአንድን ስነ - ቃል ደራሲ ለይቶ ማወቅ አይቻልም ሊባልም ቀደም ባለ ጊዜ አንድ የፈጠራ ችሎታ ያለው ሰው የፈጠረው መሆኑን እንገነዘባለን። የግለሰቡ ኪናዊ ፈጠራ አሻራም እንዳለበት ግልፅ ነው። ስነ - ቃሉን አንዱ ሰምቶ ለሌላ የሚነገረው የሚተረተው ወይም የሚዜመው ደግሞ የራሱን ፈጠራ በመጨመር ለሌላ ያስተላልፈዋል። ከዚህ የተነሳ ስነ -ቃል ብዙ ህልውና አለው ይባላል።

ምንጭ፦ ዘሪሁን አስፋው። የስነ - ፅሑፍ መሰረታዉያን።

ሀ/ ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የስነ - ቃል ምንጭ የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጠመኞች ናቸው። ሲል
   A. ስነ - ቃል በአጋጣሚ የሚፈጠር ነው።
   B. የስነ - ቃል ምንጩ የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ መስተጋብሮች ናቸው።
   C. ስነ - ቃል ሳይፈለግ የተፈጠረ ነው።
   D. ስነ - ቃል ታስቦ መፈጠር አለበት።
2. ከሚከተሉት አንዱ የስነ- ቃል ተግባር አይደለም።
   A. ሕዝቦች ማንነታቸውን ያሳውቁበታል።
   B. የዝርያቸውን አመጣጥ መተረክ
   C. የሒሳብ ቀመሮችን መፍጠር
   D. ፍልስፍናቸውን መቅረፅ።

3. በቅርፅ ከሁሉም የሚለየው
A. ምሳሌያዊ አነጋገር B. ባህላዊ ዘፈን C. እንቆቅልሽ D. ተረት
4. ሥነ - ቃል --------- በማይገለገሉ ሁበረተሰቦች የበለጠ ያገለግላል።
A. ስርዓተ ፅሀፈት B. ንግግር C. ቋንቋ D. ምልክት
5. ስነ - ቃል የሚተላልፍበት መንገድ
A. በመናገር B. በመተረት C. በመዜም D. በሁሉም
6. የመጀመሪያው አንቀፅ ዋና ሀሳብ
A. ስነ - ቃል በቃል የሚተላለፈ ኪነ - ጥበብ ነው። C. ስነ- ቃል የብዙ ገጠመኞች ጥርቅም ነው።
B. ስነ - ቃል በፅሑፍ መቅረት አለበት። D. ስነ - ቃል የሕዝብ ሀብት ነው።
7 . -------- ከስነ - ቃል ባህሪያት አንዱ ነው።
A. ወደ ፅሑፍ ሊቀየር አለመቻሉ። C. ደራሲው አለመታውቁ
B. በፅሑፍ መተላለፍ። D. A እና B
8. ስነ - ቃልን የፈጠሩ ሰዎች የትኛውን ሊያሚሉ ይችላሉ?
A. በግልፅ/ በስም/አይታወቁም C. ላቅ ያለ ኪ ናዊ ፈጠራ ችሎታ ያላቸው ናቸው።
B. የፈጠራ መብታቸው ተከብራል D. ሁሉም
9. ማንፀባረቂያ /በመጀመሪያው አንቀፅ/ አውዳዊ ፍቺው
A. ማብረቀረቂያ B. ማፍለቂያ C. ማሳያ D. ውጤት
10 . ፍልስፍና ይቀረፅበታል። /ሁለተኛው አንቀፅ/ አውዳዊ ፍቺ
A. ይፈለፍላሉ B. ምስል ይስራሉ C. ያሳያሉ D. ይሰጣሉ
11. ወግና ልማድ በፍቺ
A.ተቃራኒ ናቸው B. አይመሳሰሉም C. ተመሳሳይ ናቸው D. መልሱ የለም
12. ሰናይ /ሁለተኛ አንቀፅ ተመሳሳዩ
A. መልካም B. በጐ C. A እና B D. መጥፎ
13 . የስነ - ቃል አበይት ባህሪያት ውስጥ የሚጠቀሰው
A. ተለዋዋጭነት B. ደራሲው አልታወቀም C. A እና B D. ከአንግዲህ የማይፈጠር መሆኑ
14 .በሁለተኛው አንቀፅ ከተጠቀሱት ቃላት የሚቃረኑት
A. እኩይና ሰናይ B. ድጋፍና ተቃውሞ C. ወግና ልማድ D. A እና B
15. የመጨረሻው አንቀፅ ሀይል ቃል --------- ይገኛል።
A. በመጀመሪያ B. በመሀል C. በመጨረሻ D. በመጀመሪያና በመጨረሻ
16. የመጀመሪያው አንቀፅ ዋና ሀሳብ
A. ስነ - ቃል በቃል የማተላለፍ ኪነ - ጥበብ ነው። C. ስነ - ቃል የብዙ ገጠመኞች ጥቅም ነው።
B. ስነ - ቃል በፅሑፍ መቅረት አለበት። D. ስነ - ቃል የሕዝብ ሀብት ነው።

<u>ለ/ ተመሳሳይ ፍቻቸውን መርጣችሁ መልሱ።</u>

17. ትንቢት
A. ያለፈ ጊዜ B. የወደፊት ጊዜ C. የማይታወቅ D. የማይታይ
18. ህዳሴ
A. ኋላቀር B. አዲስ ስርዓተ C. መጪ ጊዜ D. ዛሬ
19. መባቻ
A. የወር መጀመሪያ B. የጦርነት ጊዜ C.መጠጫ D. መቆሚያ
20. ዘበት
A. አወቀ B. ዘመን C. ቧልት ያዘ D. ቀደመ
21. አበጀ
A. ሰራ B. ከበበ C. ቆረጠ D. ሰጠ

<u>ሐ/ የተሰመረባቸውን ፊሊጣዊ አነጋገሮች ፍቺ ከተሰጡት አማራጮች መካከል መርጣችሁ መልሱ።</u>

22. የአለማየሁ እህት <u>ደመ ግቡ</u> ናት።
A. ሀብታም B. ተናዳጅ C. ቆንጆ D. የሰከነች
23. እንደዚያ ደክሞ ደክሞ <u>መና ቀረ</u>።(አለፊለት B. አጣ C. የልፋቱን አገኘ D. ሀብታም ሆነ
24. ይኼ ልጅ <u>የጥርስ ስጋ</u> ሆነብኝ።
A. ነዝናዛ B. ለስላሳ C. የዋህ D. ታማሚ
25. ይህችን <u>ቆሞ ቀር</u> ምናለ አንድ በሏት።
A. ገታራ B. ተጫዋች C. ቶሎ የላገባች D. ወሬኛ
26. ታቦቱን ለማንገስ የከተማው ሕዝብ <u>በነቅስ</u> ወጣ።
A. ተመርጦ B. በቀስቃሽ C. በሙሉ D. ጥቂት
27. ያንን <u>በገፈጅ</u> ወዲህ አስጠጋልኝ።
A. አልቅሺ B. ተደባደበ C. ሰፊ ድስት D. ተኩላ
28. ለቅሶ ቤት ሔጄ፣ <u>ግንባሬን አስወግቼ</u> ልምጣ።
A. መምሬን አሳውቁ ታምቼ C. አልቅሺ D. ደብድቤ
29. ሰውዬው በተኛበት <u>ሰተት ግጥም</u> አለ።
A. ሞተ B. ታመመ C. አደ ደረሰበት D. ተከሰከሰ
30.የተሰቀለ ቋንጣ አይቶ <u>ለየ</u>።
A. ጐመዠ B. ሰረቀ C. በላ D. ተናደደ
31. ይሔን <u>ክትክታ ነቃይ</u> ውድምሽን ስርዓት አሳይቸው።
A. ደካማ B. ብርቱ C. ባለጌ D. ጉልበተም

<u>መ/ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን የሚያሟሉትን መርጣችሁ መልሱ።</u>

32. ለተቀማጭ ----------
A. ሰማይ ቅርቡ ነው B. ቤቱ አይመች C. ገንዘብ ቀማኛ D. ጥሩ አድማጭ
33. ---------- ለባሏ ዘውድ ናት።
A. የንጉስ ሚሰት B. ቆንጆ ሴት C. ሩህሩህ እናት D. መልካም ሴት
34. ላም ባልዋለበት ----------
A. ይገኛል B. አይገኝም ኩበት C. ኩበት ለቀማ D. ዋለ

35. ልፋ ያለው ----------
A. በህልሙ ዳውላ ይሸከማል B. ከድንጋይ ይታገላል C. ግድግዳ ይገፋል D. ይጋረጣል
36. ------- ተያይዞ ቆላ
A. ገበዝ በጐበዝ B. ጅልና ጅል C. ማሽላ ለማሽላ D. የአገር ልጅ በሞላ

37. ሰውና እንጨት ----------
A. ይደጋገፋሉ B. ጠላት ናቸው C. ተስባሪ ነው D. ጠንካራ ናቸው
38. የማይታማመን ባልንጀራ ----------
A. አብሮ አያድርም B. በየወንዙ ይማማላል C. ይገዳደላል D. አያዛልቅም
39. --------- ሲበሉት ያቅራል።
A. ትኩስ ምግብ B. ገንፎ C. ሲያዩት ያላማረ D. ያደረ ምግብ

<u>ሠ/ ከታች ለቀረቡት ቅኔዎች ወርቁን የያዙትን በመምረጥ መልሱ።</u>

40. እዚያ ላይ ሆነህ ከተራራ
ሰው ከንቱ ብለህ ጥራ
A. ሰው ከንቱን ጥራልኝ C. የሰውን ከንቱነት ተናገረ
B. ከንቱ ስለሆንክ ጩኽ D. ተራራ ላይ ወጥተህ ብሶትህን አሰማ
41. ሚስቱ በያይነቱ ቁርስ ስትሰጠኝ፣

ቅንጨዋ ናት በጣም የምስስማማኝ።
A. ቅንና ጨዋ ሴት ናት B. ቅንጨዋ ይጣፋጣል C. ቁር ታበላኛለች D. ባለሞያ ናት
42. ቁጠባ ሳናደርግ ተሻምተን በልተን፣
እነኛ ወጥ አጡ እኛ እንጀራ አጣን።
A. ስንበላ እንጀራና ወጥ አጣን C. እነሱ ከፍ ከፍ ሲሉ እኛ ድሆች ሆንን
B. ቁጠባ ስላደረግን ተቸገርን D. ወጥ ስለተቸገሩ እናበድራቸው
43. እያነጋገረኝ ሊጠይቀኝ ወሬ፣
አለም ብሎ ነው አለመናገሬ።
A. መልሱን አላውቅም C. ወሬ አልወድም
B. ካለ አቅሜ/ደረጀዬ/ ብሎ ነው D. የማላውቀውን ጉዳይ አልዘላብድም
44.የሰጡትን እቃ ቁጥሮ ካላኖር፣
ታጣ ወዳጅነት ዘመድ መሆን ቀረ።
A. የአደራ ዕቃ መቀመጥ አለበት C. ዘመድ ሲቸገር መርዳት ይገባል
B. ወዳጅ መሆን ቀርቷል D. የተቸገረ ሰው ዘመድ የለውም

<u>ረ/ ከዚህ በታች የቀረቡትን የተለያዩ ጥቃቄዎች እንደሁኔታው መልሱ።</u>

45. ትክክለኛ ስርዓተ ነጥብ የተጠቀመው ዓረፍተ ነገር
A. ልጁ "ዛሬ ልደቴ ነው? " ብሎ ተናገረ። C. ልጁ "ዛሬ ልደቴ ነው !" ብሎ ተናገረ።
B. ልጁ "ዛሬ ልደቴ ነው? " ብሎ ተናገረ። D. ልጁ "ዛሬ ልደቴ ነው። " ብሎ ተናገረ።
46. የስርዓተ - ነጥብ ተግባር ያልሆነው?
A. ተጨማሪ ሀሳብ መግለፅ C. በፅሑፍ ውስጥ ስሜትን መግለፅ
B. ትክክለኛ ትርጉም መስጠት D. ለ ና ሐ መልስ ናቸው

47. ከሚከተሉት አንዱ የድርብ ዓ.ነገር ትዕምርት ጥቅስ ተግባር አይደለም
A. አድናቆትን ማሳየት C. እንግዳ ቃላትን ማሳየት
B. የሌላ ሰው ንግግር ማሳየት D. ልዩ ትኩረት የሚሰጡትን ማሳየት
48. ክርክር ከውይይት የሚለየው
A. ማራኪ አለባበስ ማስተናገዱ C. ስርዓት ያለው መሆኑ
B. ለማሸነፍ የማደረግ ትግል መሆኑ D. በጊዜ የተመጠነ መሆኑ
49. በክርክር ጊዜ
A. ማስታወሻ ይዞ ማንበብ ይቻላል።
B. ማስታወሻ መያዝ አይቻልም።
C. ዋና ሀሳቦችን በወረቀት መያዝ ቢቻልም ማንበባችን መታወቅ የለበትም
D. የምናቀርበውን ሀሳብ በሙሉ መያዝ አለብን
50. መስተዋድዳዊ ሀረግ የያዘው የቱ ነው?
A. በጣም አጭር B. እንደ ወንድሙ C. ድንገት D. ተውሳከ ግስ
51. ″የወጣው ልጅ ≡ የሐረጉ አይነት
A. ስማዊ B. ግሳዊ C. ቅፅላዊ D. ግሳዊ
52. ትንሽ እውነት ይዞ አተልቆና አግዝፎ የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት የቱ ነው?
A.ምፀት B.ሰውኛ C. አነፃፃሪ D. ግነት
53. መምህራችን <u>እክል</u> ገጠማቸው። የተሰመረበት ቃለ ተመሳሳይ ፍቺው
A. ችግር B. ደስታ C. ቀጠሮ D. ታሞ
54. በአንድ አንቀፅ ውስጥ ያለውን ሀሳብ አጠቃሎ የያዘ ዐ.ነገር ምን ይባላል።
A.ዝርዝር B. ፅሑፍ C. ተራ ዓ.ነገር D. መሪ ዓ.ነገር
55. ባልና ሚስት <u>ፊርማ ቀደዱ።</u> የተሰመረበት ቃል ፍቺ
A. ተፋቱ B. ተጣሉ C. ተስማሙ D. ምንኩስናዉን አፈረሱ
56. በሚዳው ላይ ነጭ ፍየል ይታያል። የስም ገላጩ
A.ላይ B. ነጭ C. ከሚዳው D. ፍየል
57. በድርሰት አካላት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

A. አስተዋፅኦ B. መግቢያ C. ሀተታ D. ርዕስ

58. በውስጡ አንድ ግስ ብቻ የሚይዝ የዐረፍተ ነገር ዓይነት ምን ይባላል?

A. ተራ B. ውስብስብ C. ትዕዛዛዊ D. አገናኝ

59. <u>ወደ</u> መማሪያ ክፍለ ሒደ። የተሠመረበት ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል።

A. ግስ B. መስተዋድድ C. ቅፅል D. ስም

60. በልቦለድ ከቀረበው ታሪክ ውስጥ በዋናነት የሚተላለፈው ፍሬ ነገር ምን ይባላል?

A. ገፀ ባህሪ B. ጭብጥ C. ግጭት D. መቼት

አዘጋጅ፡ መ/ር እንግዳ አየለ